===============================////\\\\===============================

# አቶ ስዬ ከሃራምቤ ጋዜጣ ጋር

«ትግል የበቃኛል ማለትን ሕሊናዬ አይቀበለዉም" በሚል አርዕስት በኢትዮጵያ የሚታተም ሃራምቤ ጋዜጣ በረብዑ ሰኔ 25 2000 ዓ.ም ዕትሙ ከቀድሞ የመከላከያ ሚኒስቴር ከነበሩትና በኢሕአዴግ 6 አመት ታስረዉ ከተፈቱት ከአቶ ስዬ አብርሃ ጋር ያደረገዉን ቃለ ምልልስ አዉጥቷል። የቃለ ምልልሱን ሙሉ ይዘት እንደሚከተለዉ አቅርበንላቹሃል።

**ሃራምቤ - በቅርቡ መድረክ ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ምክክር የሚባል ትብብር መሰርታችኋል። የዚህ መድረክ ዓላማ ምንድን ነዉ?**

አቶ ሰዬ - እንደሚታወቀዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። ነገር ግን ጥንካሪያቸዉ እንደብዛታቸዉ አይደለም። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ለዉጥ ለማምጣት ከተቃዋሚዎች በኩልም ጠንካራ ተፎካካሪ እና የተሻለ አማራጭ ሆኖ መቅረብ የግድ ይላል። በርካታ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩም በመሃከላቸዉ ጠንካራ ትብብር አይታይም። አንዳንድ ጊዜ ትብብር ይሞከራል፤ እንደገና ትብብር ይበላሻል። የእኛ ትብብር መድረክ በዋናነት የዉይይት መድረክ ነዉ።

**ሃራምቤ - የውይይይት መድረክ ሲሉ ?**

አቶ ስዬ - የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ አቋም አላቸዉ። በዚህ አቋማቸዉ የሚቀራረቡበት ሁኔታ አለ። የሚቀራረበዉ አቋማቸዉ ተለይቶ እንዲወጣ፣ የሚለያያቸዉ ጉዳይም ተለይቶ እንዲወጣ ማድረግ ነዉ። ስለዚህ ልዩነታቸዉን በሚያቀራርባቸዉና በሚያስማማቸዉ ጉዳዮች ላይ የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም ነድፈዉ፣ በዚህ ፕሮግራም ዙሪያ አንድ ፖለቲካዊ ማእቀፍ - ግንባር በለዉ ቅንጅት በለዉ - ፈጥረዉ በተሻለ ጥንካሬና ጥራት ሊቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ነዉ። ከዚህ ዓላማ በመነሳት ይሄ መድረክ ሥራ ጀምሯል። በሂደት አጀንዳዎች እያስቀመጠ በነዚህ አጀንዳዎች ዙሪያ ይወያያል። በዉይይቱ ወቅት ስምምነት የሚደረሰባቸዉን ፕሮግራም የሚቀረጽበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

**ሃራምቤ- ይህን መድረክ ለመመስረት ምን ያህል ጊዜ ፈጀባችሁ ?**

አቶ ስዬ - አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲዚህ የጋራ መድረክ ፈጥረዉ የመስራት አስፈላጊነት ላይ እየተመካከሩ ቆይተዋል። በእያንዳንዱ ሰዉ ጭንቅላት ዉስጥ ሲብላላ የቆየ ነዉ። አሁን መድረኩን የመሰረቱት ፓርቲዎችና ግለሰቦች ቁጭ ብለዉ መነጋገር ከጀመሩ 2 ወር ያህል ቢሆን ነዉ። ዋናዉ ቁም ነገር ወደፊት የመቀጠል ስራ ነዉ።

**ሃራምቤ - መድረኩን የፈጠራችሁት ፓርቲዎች እና ግለሰቦች ናችሁ፡ ሕብረት፣ አፍዴን፣ ሶደህን፣ አረና ፓርቲዎች እንዲሁም እርስዎና ዶ/ር ነጋሶ ናችሁ። እርስዎና ዶ/ር ነጋሶ እንደ ፓርቲ ነዉ የምትቆጠሩት ወይስ ?**

አቶ ስዬ - አዋ አራት ፓርቲዎች ናቸዉ መድረኩ ዉስጥ ያሉት። ሕብረት በዉስጡ ሶስት ፓርቲዎች አሉት። አፌደን አለ። አረና ትግራይ አለ። የሶማሌ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ አለ። ሁለት ሰዎች ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ተሳትፈናል።

ከላይ እንደገለጽኩልህ ይሄ ጥምረት አይደለም። የምክክር የዉይይት መድረክ ነዉ። በግለሰብ ደረጃ በዚሁ የዉይይት መድረክ መሳተፍ የሚከለክል ሕግ የለም። ሙብታችን ነዉ። «የግሰቦች በእንደዚህ ያለ የዉይይት መድረክ መሳተፍ ፋይዳዉ ምንድን ነዉ?» የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። እንደምታዉቀዉ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ መግባት የራሱ ችግርና ጣጣ አለዉ። በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ ሰዉ ቆጠብ የማለት ሁኔታ አሳይቷል። ይሄ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነዉ። ሆኖም በፖለቲካ ፓርቲ ተደራጅተዉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች አሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ሁሉ በፓርቲዎች ዉስጥ ታቅፈዋል ማለት አይደለም። በተለያዩ ምክንያት በፓርቲዎች ዉስጥ ሊታቀፉ ያልቻሉ በሳል ፖለቲከኞች፣ በሳል ምሁራን ኢትዮጵያ ዉስጥ አሉ። እነዚህ ሰዎች በእንደዚህ ያለ መድረክ ተሰብስበዉ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በማስተካከልና በማቅናት፣ መግባባት በመፍጠር በኩል የራሳቸዉን አዎንታዊ ድርሻ ሊጫወቱ ይችላሉ።

ይኼ መድረክ በፓርቲ ዉስጥ ከተደራጁት ዉጪ ለግለሰቦች ለቡድኖች ክፍት መሆኑ ጥሩ ነገር ነዉ። የቆዩ የፖለቲካ ሰዎች እና ምሁራን ከፓርቲዎች ጋር በመመካከር አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲጫወቱ እድል ያገኛሉ። ስለዚህ ይሄ እድል፣ ይሄ መስኮት መከፈቱ ጠቃሚ ስለሆነ ነዉ ግለሰቦችንም ፓርቲዎችንም እንዲያካትት የተደረገዉ።

በመግለጫችን ላይ እንዳሰፈርነዉ ያስቀመጥናቸዉ መርሆች አሉ። እነዚህን መርህዎች የሚቀበሉ እና አስተዋጽኦ ያደረጋሉ የተባሉ ፓርቲዎች ቡድኖችና

ግለሰቦች በመድረኩ አባላት ስምምነት አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

**ሃራምቤ- ምን ምንድን ናቸዉ ምርህዎቹ ?**

አቶ ስዬ - መርህዎቹ በርካቶች ናቸዉ። ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባት እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፍትህ የሰፈነባት፣ በብሔር በሔረሰቦች እኩልነት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን መገንባት፣ ነጻና ገለልተኛ ምርጫ ተደረጎ የሕዝብ የበላይነት በተግባር እንዲገለጽ፣ በነጻ የመደራጀት የመናገር የመጻፍ መብት እንዲከበር፣ የግለሰብ የብሄር የብሄር ብሄረሰቦችና የቡድን መብቶች በተጓዳኝነት እንዲከበሩ፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የሚቆም .... እነዚህን የመሳሰሉ መርህዎችን የሚቀበሉ እና የመድረኩ አባላት በጋራ ስምምነት የተቀበሏቸዉ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ድርጅቶች ሁሉ ይካተቱበታል።

**ሃራምቤ -እርስዎ እስከአሁን ድረስ በግልዎ ነዉ እየተንቀሳቀሱት ያሉት።፡ለምን የአንድ ፓርቲ አባል አይሆኑም። ለምሳሌ የአረና ?**

አቶ ስዬ - የመፈለግ ያለ መፈለግ ጉዳይ አይደለም። የትኩረትና ቅድሚያ የመስጠት ጉዳይ ነዉ። ይሄ ማለት ምን ማለት ነው ? አሁን ባለዉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሜዳ፣ የፖለቲካ ገበያ እንበለዉ በርካታ ድርጅቶች አሉ። በዚህ ሜዳ ዉስጥ «የተሻለዉ መንገድ የትኛዉ ነዉ?» ብዬ ነዉ የማስበዉ። እኔም ፈጠርኳቸዉ ሌሎች ፓርቲዎች፣ ፓርቲዎች አሉ። የግድ እኔ የመሰረትኩት ወይም ያለሁበት ፓርቲ አባል መሆን አይደለም ቁም ነገሩ። ስለዚህ አሁን ባለዉ ሁኔታ «ለሀገራችን ጠቃሚና ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባዉ አቅጣጫ የትኛዉ ነዉ ?» የሚለዉ ጥያቄ መመለስ አለበት።

በእኔ እምነት ዋናዉ ነገር ፖለቲከኞች የሚስማሙበት የጋራ ፖለቲካዊ አቋም መኖሩ ነዉ። የጋራ የፖለቲካ ፕሮግራም መኖሩ ፣ የጋራ የትግል ስትራቴጂና ስልት መኖሩ ነዉ ወሳኙ። በግልሰብ ደረጃም ይሁን በፓርቲ ዉስጥ ያለን ፖለቲከኞች ዋናዉ ችግራችን አብዛኛዎቻችን ልንስማማበት የምንችል የጋራ ፖለቲካ ፕሮግራም መቅረጽ አለማቻላችን ነዉ። የሚያስማማን የጋራ ስትራቴጂና ስልት ያለመኖሩ ነዉ። እነዚህን ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ከተደረሰ የጋራ መታገያ መድረክ ይፈጠራል ማለት ነዉ።

ለዚህ ጉዳይ መሥራት ቅድሚያ ሊሰጠዉ ይገባል የሚል እምነት ስላለኝ ነዉ አንድ ፓርቲ ዉስጥ መግባት ወይም እኔ የምመራዉ ፓርቲ ለመመስረት ያልፈለኩት።

**ሃራምቤ - ኢትዮጵያ ዉስጥ በተለያዩ ጊዜ ምድረክ፣ ትብብር፣ ቅንጅት ..የሚባል ነገር ይፈጠራል። ወዲያዊ ይፈራርሳል። ይሄ መድረክ ምን ያህል ጽናት ይኖረዋል ብለዉ ያስባሉ ?**

አቶ ስዬ - እንግዲህ በተቃዋሚ ፓርቲነት ተደራጅተዉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ የተቃዉሞ ፖለቲካ ያለፈበትን መንገድ፣ ዉጣ ዉረድን አይተናል።ስለዚህ እነሱ ለዚህ መድረክ የሚጠቅም፣ ካለፉበት ሁኔታ የተማሩት ትምህርት አለ። ባለፈዉ የተቃዉሞ ፖለቲካ ትግል ዉስጥ ያልነበርን አለን። እኛ ደግሞ የራሳችን ልምድ ይዘን እንመጣለን።ካለፈዉ ልምድ በመነሳት አሁን ባለዉ አጠቃላይ ሁኔታ ሁላችንም ጋር «ሲሮጡ የታጠቁት፣ ሲሮጡ ይፈታል» የሚል ግንዛቤ አለን። በዚህ የተነሳ ነዉ «በመጀመሪያ የዉይይት መድረክ ብለን እንጀምረዉ» ወደ ማለት የገባነዉ።

ፓርቲዎችም እኛ ግለሰቦችም የተለያዩ አቋሞች አሉን። በነዚህ አቋሞቻችን ላይ እንወያያለን። ስንወያይ ነዉ አቋሞቻችን ሊሸጋሸጉ የሚችሉት። ይሄንን ስናደርግ ወደ ሕብረት ወደ ቅንጅት ወደ ግንባር መምጣት እንደማይሰራ ሁላችንም ግንዛቤ ወስደናል። ስለሆነም ይሄ መድረክ ለየት የሚያደረገዉ አንደኛ ካለፈዉ የተገኘ ትምህርት አለ። ሁለተኛ «በዉይይት አቋማችንን ተገላልጠን የሚያስማሙን ጉዳዮች መለየት አለብን» ብለን ነዉ የወሰንነዉ። አሁን ያለዉ እዉነት ዉይይቱ መጀመሩ ብቻ ነዉ።

**ሃራምቤ - በሰላማዊ ትግል ዉጤት አይመጣም የሚሉ ሰዎች አሉ። በሰላማዊ ትግል ዉጤት እናመጣለን ብላችሁ ታማንላችሁ?**

አቶ ስዬ - ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የፖለቲካ ምህዳር አስቸጋሪ ነዉ። ገዢዉ ፓርቲ የሰላማዊ ትግል ለማካሄድ ሕገ መንግስቱ ከሚያስቀምጠዉና ከሚለዉ በተለየ ሕጎችን እየወጣ ፖለቲካዊ ምህዳሩን እያጠበበዉ ነዉ። በዚህ የተነሳ እዉነተኛ ተቃዋሚ መሆን አስቸጋሪም አደገኛም ነዉ።

«ይሄ ስለሆነ ትግል ይተዋል ወይ ?» ነዉ ጥያቄዉ ። ትግሉ መተዉ የለበትም። የሚሻለዉ አቅም እንዳይበታተን፣ ትኩረት እንዳይበታተን የተለያየ ፖለቲካዊ ፕርግራም ያላቸዉ ኃይሎች ተባበረዉ በሚያስማማቸዉ ጉዳዮች ላይ የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም ቀርጸዉ ሕዝቡን ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚያነቃንቁበት ሁኔታ መፍጠር ነዉ። የተናጥል ትግልን፣ የተበታተነን ትግልን አስወግዶ መታገል ነዉ እንጂ ተስፋ ቆርጦ ከትግል መዉጣት. በኢትዮጵያ ተስፋ መቁረጥ ማለት ነዉ። ይሄ መንገድ በሚገባ ተሰርቶበት፣ በሚገባ ታስቦበት ወድቋል የሚል እምነት የለኝም።

===============================////\\\\\===============================

የተናጥል ትግል መቆም አለበት። ይኼንን እዉነት ተገንዝበዉ መተባበር ሲጀምሩ፣ አንድ ኃይል ሆነዉ መቅረብ ሲችሉ፤ ሕዝብን ከጫፍ እስከ ጫፍ ማንቀሳቀስ ይችላሉ። ያኔ አንዱ ሲነሳ አንዱ የሚተኛበት ሁኔታ አይፈጠረም።

ትብብርን ማሳካት እስከአሁን አልተቻለም። ማሳካት ከተቻለ ግን ሰለማዊ ትግሉ ተስፋ የለዉም ማለት አይቻልም። ቁጭ ብለዉ ተነጋግረዉ ሃሳቦቻቸዉን አሸተዉ ከገቡበት፣ ሰላማዊ ትግል የማይሳካበት ሁኔታ አይታየኝም።

በእኔ እምነት ሰላማዊ ትግል ማለት ምርጫ ሲደርስ የሚደረግ «ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ» አይደለም። ሰላማዊ ትግል ምርጫ ቢኖርም ባይኖርም ፖለቲካዊ ምህዳሩን ለማስፋት የሚካሄድ ነዉ። በሕገ መንግስቱ የሰፈሩት ሰብዓዊ ፖለቲካዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ በየጊዜዉ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን እየተቃወሙ ምህዳሩን ለማስፋት የሚደረግ የዕለት ተዕለት ትግል ነዉ። በዚህ አድማስና ስፋት ሰላማዊ ትግሉ ከተኬደበት ዉጤት የማይመጣበት ምክንያት የለም።

**ሃራምቤ - መድረኩ መመስረቱን አስመልክታችሁ ባወጣችሁት መግለጫ ላይ ዓለም አቀፍ ድጋፍ እንደምትሹና ዲፐሎማሲያዊ ጥረት እንደምታደርጉ ወዘተ ገልጻቹሃል። ይሄ አባባል «የተቃዉሞ ኃይሎች በዉጭ ኃይሎችና በዲያስፖራዉ የሚጠመዘዙ መሆናቸዉን አመላካች ነዉ» የሚሉ አሉ። የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነዉ ?**

አቶ ስዬ - እንደኛ ነገር አሁን የመግለጫዉ ክፍል መድረኩ ሊሰራቸዉ ይገባል ተብሎ ከተዘረዘሩት አምስት ነጥቦች አንዱ ነዉ። መድረኩ አምስት ግቦች አሉት። ከግቦቹ ዋነኛዉ ዉይይት ማካሄድ ነዉ። ይሄ የጠቀስከዉ አምስተኛዉ ግብ ነዉ። ዓለም አቀፍ ድጋፍ መሻትና ዲፐሎማሲያዊ ጥረት ማድረግ የትግሉ አካል እንጂ ዋናዉ ትግል አገር ዉስጥ የሚደረገዉ ነዉ። በፓርቲዎች መሀከል መቀራረብ ለመፍጠር የሚደረገዉ ትግል፣ የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገዉ ወዘተ ነዉ ዋናዉ። ያም ሆኖ የዲፖሎማሲያዊ ጥረት አስፈላጊ ነዉ።

የዲፐሎማሲ ትግል ሲባል በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዙሪያ ለዲፖሎማቲክ ኮምኒቲዉ ያለዉን ሁኔታ ማሳየት ነዉ። በነገራችን ላይ እነሱም «ተቃዋሚዉ ራሱ አይተባበርም» የሚል አስተያየት አላቸዉ። «ተቃዋሚዉ እርስ በርሱ ይናናቃል» የሚል እምነት አላቸዉ። ስለዚህ አሁን ተቃዋሚዎች የምክክር ሥራ መጀመራቸዉን ማሳወቅ የዲፐሎማሲዉ ትግል አካል ነዉ። ከዚህ ባሻገር የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲሰፋ የሚቻላቸዉን ያህል ድጋፍ እንዲያደረጉ መጣር ነዉ።

ልክ እንደዚያዉ ሁሉ የዲያስፖራዉ ድጋፍ በዚህ አይነት እንቅስቃሴ የራሱ በጎ አስተዋጽኦ አለዉ። የነሱንም ድጋፍ ማግኘት ተገቢ ነዉ። ነገር ግን የተቃዉሞ ፖለቲካዉ በዲያስፖራዉ ይጠመዘዛል የሚለዉ በኛ መድረክ ተቀባይነት የለዉም።

የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ገጸ-ምድር ሊለወጥ የሚችለዉ ሀገር ዉስጥ በሚደረግ ትግል ነዉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያደርገዉ ትግል ዉሳኔና ፍላጎት ነዉ የሚመረኮዘዉ። 80 ሚሊዮን ሕዝብ እዚህ እያለ፣ ምርጫ ሲመጣ ቁር እየፈጀዉ ተሰልፎ ድምጹን የሚሰጠዉ ሕዝብ እያለ፣ መታሰር መገረፍ ሲመጣ የሚታሰረዉ የሚሰቃየዉ እዚህ እያለ፣ የዚህን ሕዝብ ይሁንታዉን ሳያገኙ በኢትዮጵያ ዉስጥ ፖለቲካዊ ለዉጥ አመጣለሁ ብሎ መከጀል የፖለቲካ የዋህነት ነዉ። እንደዚህ የሚያስቡ ካሉ ተሳስተዋል። እንደዚህ የሚያስቡ ፓርቲዎች አሉ ወይ ? አላዉቅም። በዚህ መድረክ ያሉት እንደዚህ ያስባሉ ብዬ አላምንም።

ይህ ሲባል የዲያስፖራዉን ድጋፍ ማጣጣል አይደለም። እንደሚመስለኝ የዲያስፖራዉ ፍላጎት በሀገራቸዉ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን እንጂ፣ ከዚህ የተለየ ፍላጎት ያላቸዉ አይመስለኝም። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ገጸ ምድር እንዲቀየር በመሬቱ ላይ፣ በሀገር ዉስጥ ሆነዉ የሚታገሉትን የፖለቲካ ኅይሎች መደገፍ ነዉ ስራቸዉ። እነሱን ተከትለዉ እንሂድ ቢሉ ብዙ የሚያስኬድ አይመስለኝም። እነሱን ተከተዉ መሄድ የሚፈልጉ ኃይሎች አሉ ወይ? እኔ አላዉቅም። ካሉ ግን ተሳስተዋል።

**ሃራምቤ - ከዕስር ከተፈቱ በኋላ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ያልተዋጠላቸዉ ወገኖች «ስዬ አብርሃ ሕወሃትን ለማፍረስ እየሰራ ነዉ»...ሌላም ሌላም እያኑ ነዉ። እርስዎ በዚህ ላይ ምን ምላሽ አልዎት ?**

አቶ ስዬ - አዎ እንደዛ ይባላል። በጥር ወር አካባቢ ለፓርቲዉ አባላት የተሰራጨ ወረቀት ነበር። «እነ ስዬ፣ እነ አረና ከጠላቶቻችን ጋር እየሰሩ ነዉ» የሚል። «ከትግራይ ሕዝብ ጠላቶች ጋር እየተባበሩ ነዉ» የሚል ነገር አለ። «ተከታተሏቸዉ። ሰልሏቸዉ» ነዉ የሚለዉ። አዝናለሁ። ሕወሃት የስለላ ድርጅት እንዲሆን በመጠየቃቸዉ።

እኔ እንደተገነዘብኩት በፓርቲዉ አባላት ሳይቀር ይሄ ተቀባይነት ሊያገኝላቸዉ አልቻለም። አሁን ገዢዉ ፓርቲ ዉስጥ ያሉትን ሰዎች የሚያቃቸዉን ያህል እኛንም የትግራይ ሕዝብ ያወቀናል። በእኔ እምነት የትግራይ ሕዝብ አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችለዉ ከኢትዮጵያ ወገኑ

ሲነጠል ነዉ። ከወገኑ ተለይቶ ሲታይ ነው። ባልበላበት የበላ፣ ባልተጠቀመበት የተጠቀመበት ሆኖ ሲታይ፣ ራሱ በገዢዉ ፓርቲ ተገፊ ሆኖ እያለ ልዩ ጥቅም እንደሚገኝ ተደርጎ በጥርጥሬ ሲታይ ነዉ የትግራይ ሕዝብ የሚጎዳዉ። ይሄ ጉዳት ሊደርስበት የሚችለዉ ደግሞ በገዢዉ ፓርቲ ፖለቲካ እንጂ እኔ ወይም አረና በምናደረገዉ ፖለቲካ አይደለም።

እኔም ሆንኩ አረና የኢትዮጵያ ሰላም ዲሞክራሲ የኢትዮጵያዉያን የእርስ በርስ ፍቅርና ግንኙነት ያስጨንቀናል። ያሳስበናል። ስለዚህ ይሄ ነገር መልክ እንዲይዝ ከወንድሞቻችን ፖለቲከኞች ጋር አብረን እየሰራን ነዉ። ይሄ ሁኔታ ከተስተካከለ ማንም ኢትዮጵያዊ አይጎዳም። የትግራይ ሕዝብም አይጎዳም።

አሁን እኛ እየስራን ያለነዉ የትግራይ ሕዝብም ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በሀገሩ ጉዳይ፣ በኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታ በትግሉ ዉስጥ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ማገዝ ነዉ። ይሄ ትብብር የሚያስፈራዉ ገዢዎችን እንጂ የትግራይን ሕዝብ ሊሆን አይችልም። ሁላችንም ተቃቀፈን፣ ተከባብረን የምንኖርባት፣ አሁን ያለዉ ስጋት የሚቀረፍባትን ሁኔታ ለመፍጠር የምንሰራበት መድረክ ነዉ።

***ሃራምቤ - እርስዎ አሜሪካ በሄዱበት ወቅት ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ተገናኝተዉ ነበር የሚል ወሬ ተሰምቶ ነበር። እዉነት ነዉ ?***

አቶ ስዬ - «ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ተገናኝተዋል» የሚል ዜና ሰማቻለሁ። በመሰረቱ ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ስንገናኝ ይህ የመጀመሪያችን አይደለም። ዶ/ር ብርሃኑ የአቶ ታምራት ላይኔ የልጅነት ጓደኛ ነዉ። እሥር ቤት ሳንገባ በፊት በሩቅ እንተዋወቃለን። በ93 ዓ፣ም ደግሞ እሥር ቤት ከእርሱና ከፕሮፌሰር ጋር ተገናኝተናል፡፡ከዛ በኋላ እርሱ ተፈታ እኔ እስር ቤት ቀጠልኩ። እሥር ቤት እያለሁ መጥቶ ይጠይቀኝ ነበር። እንዳንዴም ይከለክሉት ነበር። ጓደኞቼ ሲያስሩኝ እርሱ መጥቶ ይጠይቀኝ ነበር።

አሁን በ97 ዓ.ም ምርጫ ታስሮ ከተፈታ በኋላ፣ እኔም ተፈትቼ እዚህም ተገናኝተናል። አሜሪካም ተገናኝተናል። የተገናኘነዉ በዚሁ መልኩ ነዉ። ስለዚህ የተማረ ሰዉ ነዉ። አከብረዋለሁ። የፖለቲካ አቋም ልዩነት ሊኖረን ይችላል። ነገር ግን እንደማንኛዉም ሰዉ እንገናኛለን።

እነሱ ለማለት የፈለጉት «ቅንጅት ሆኗል» ለማለት ነዉ። እንኳን 97 ላይ የተሳተፈዉ ቅንጅት ልገባና ብርሃኑ ያለበት ቅንጅት የሚባል ፓርቲ የለም። 97 ላይ የተሳተፈዉ ቅንጅት እንደሌላ እናዉቃለን። «ስዬ ቅንጅት ሆነላችሁ» ብለዉ የትግራይን ሕዝብ ስሜት ለመኮርኮር የተጫጫኸ ዜና ነዉ።

***ሃራምቤ - ተራ ግንኙነት እንጂ የተለየ ግንኙነት የላችሁም ?***

አቶ ስዬ - ህእ ! ይሄን ጥያቄ ለምድን ነዉ የምትጠይቀዉ። እኔና ብርሃኑ ነጋ እኮ በአንድ ፖለቲካ መድረክ ተጣምረን አናዉቅም። እሱ ድሮም ኢሕአፓ ነበር። እኔ ሕወሃት። አሁን ደግሞ ቅንጅት ሆነ። በፖለቲካ አንድ ላይ ተቧድነን አናዉቆም። እሥር ቤት ሆኜ ለምርጫ ሲያደረግ የነበረዉን ክርክር አዉቃለሁ። በጥቅሱ የማከበረዉ ሰዉ ነዉ።

***ሃራምቤ - አቶ ስዬ አብርሃ 17 አመት ሙሉ ተዋግቷል። ከዚያም ለእሥር ተዳርጓል። አሁን ደግሞ ወደ ፖለቲካዉ ዓለም እየተመለሱ ነዉ፤ ለመሆኑ ትግል መቼ ያቆማሉ ?***

አቶ ስዬ - (ሳቅ) ገና እኮ ነኝ። አላረጀሁም።

***ሃራምቤ - በነግራችን ላይ እድሜዎ ስንት ነዉ ?***

አቶ ስዬ - 55 አመት ገደማ ነኝ። አንደኛ አንድ ነገር ከገባህበት ለመላቀቅ አስቸጋሪ ነዉ። ሁለተኛ እኔ በትግሉ ዉስጥ ከሰዎች ብዙ የጠየቅሁ ሰዉ ነኝ። ሰዎች የእኔን ቃል አምነዉ ፈንጂ እየረገጡ ተሰዉተዋል። ስለሆነም የእነሱ ዓላማ ላይ ባልደረሰበትና ባልተቋጨበት ሁኔታ እኔ ትግል ይበቃኛል ማለትን ሕሊናዬ አይቀበለዉም።

አሁን ባለዉ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እንዴት ከፖለቲካ ለመለዉጣት  ያስችላል። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁኔታ መልክ ቢይዝ ደስ ይለኛል። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ የምትገባዉ ለኑሮ አይደለም። ተቃዉሞ ፖለቲካ ዉስጥ መግባት ለእስር ፣ ለእንግልት፣ ለስደት የሚዳርግ አደገኛ ስራ ነዉ። እጠቀምበታለሁ ብለህ የምትገባበት አይደለም። በደርግም በኢሕአዴግም በቤተሰቤ ላይ የደረሰዉን መከራ እያወቅሁ ነዉ አሁንም የፖለቲካ ትግል የማደርገዉ። ይህም እንዲመቸኝ አይደለም። እየከፋኝ፣ ኑሮዬም ቤተሰቤም እየተንገላታ ነዉ ይህንን የማደርገዉ።

የሆኖ ሆኖ እኛ ከሸሸን ማን ይስራዉ ? እና ሸሽተን ሌላዉን ሰዉ አታግሉን ማለት እንችላለን ወይ ? ራሱን ገለል አድርጎ ሰዎች ይህን ለምን አያደርጉም ብለን መናገርስ ተገቢ ነዉ ወይ ? አይደለም። እኔ በዚህ መልክ ነዉ የማየዉ።

***ሃራምቤ - እርስዎ አሁን በሰላምዊ ትግል ዉስጥ ኖት። ከዚህ በፊት በትጥቅ ትግል ዉስጥ አልፈዋል።ከሰላምዊ ትግል ዉጭ አንድን ሥርዓት እንለዉጣለን ለሚሉ***

==============================////\\\\\\\\===============================

***ወገኖች ምን የሚሉት ነገር አለ ?***

አቶ ስዩ - መናገር ካለብኝ ሁለቱንም ነዉ መናገር የምፈልገዉ። በጉልበት፣ በኃይል በጠመንጃ ሕዝብን አፍኖ ስልጣን ላይ መቆየት ይቻላል የሚሉ ይሄ መንገድ ረዥም ረቀት የሚያስኬድ አይደለም። አያዛልቅምና የተሻለዉ አማራጭ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ አቻችሎ በእርቅ መንፈስ፣ በመግባባት የሀገርን ጥቅም አስቀድሞ መሄድ ነዉ። የሕብን ዉሳኔ መቀበል ነዉ የምለዉ።

እምቢ ብሏልና ከእንግዲህ ያለዉ መንገድ የትጥቅ ትግል ነዉ ለሚሉት የትጥቅ ትግልን መንገድ አዉቀዋለሁ። ትጥቅ ትግልን ዳር ለማድረስ የሚጠየቀዉን ሥራ፣ የሚያስከፍለዉን ዋጋ አይቼዋለሁ። በትጥቅ ትግል ድል ተገኝቶም በመጨረሻ ዉጤቱ ምን እንደሚሆን አይተነዋል። ስለዚህ ነዉ እኔ የሰላም መንገድ ነዉ የሚሻለዉ የምለዉ። ከእዉቀት በመነሳት ነዉ። በትጥቅ ትግል ሊገኝ የሚችለዉን ዋጋ፣ ሊከፈል የሚችለዉን መስዋዕትነት ትርፍና ኪሳራ በደንብ ስለማዉቀዉ ነዉ። የሚሰራ መሆኑን ባዉቅ ኖሮ እኔም ይሁን ባልኩ ነበር። እንደዉም አስተዋጽኦ ማድረግ የምችልበት ስለሆነ በገባሁበት ነበር። የሰላም መንገድ ነዉ የሚሻለዉ የምለዉ የጦርነትን ጣጣ ስለማዉቅ ነዉ።

አይበጅም የምለዉም ለሁለቱም ወገን ነዉ። እርስ በርስ መገዳደል ይብቃ። ኢትዮጵያ አገራችንን በእርስ በርስ መገዳደል ምክንያት ያመለጧት አጋጣሚዎች ብዙዎች ናቸዉ። በእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት በልባችን የተፈጠረዉ ቁስል ቀላል አይደለም። ያለፈዉ ቁስል እንዲያገግም እድል ሳንሰጠዉ እንደገና ወደዚህ አዙሪት መግባት፣ ሌላ ተጨማሪ እድሎች እንዲያመልጡን ያደርጋል። ቁስል እንዳይሽርና ለማስታመም አስቸጋሪ እንዲሆን ያደረጋል።

ብቸኛዉ መንገድ «የጥላቻ፣ የቂም፣ የበቀልና የሂሳብ ማወራረድን ጉዳይ አቁሞ፣ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ አቻችሎ የሀገራችንን እጣ ፈንታ ማቅናት ነዉ ። የሚሻለዉ ይሄ ነዉ» ነዉ የምለዉ። ስለዚህ «ገዢዉ ፓርቲ የፖለቲካዉን ምህዳር ማጥበቡን ይተዉና በጫካ ያሉትም ፣ በአዉሮፓና በአሜሪካ ያሉትም አገራቸዉ መጥተዉ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉበትን ሁኔታ ያመቻች። ለዚህ ተግባር ይሥራ፤ ሁላችንም ለሰላም እንስራ፤ እንተባበር፣ እንደማመጥ» ነዉ የምለዉ። በጫካ፣ በአዉሮፓና በአሜሪካም ያሉ ወገኖች ለዚህ ተግባር ይሥሩ።

***ሃራምቤ - በመጨራሻ የሚሉት ነገር ካለ ?***

አቶ ስዩ - መናገር የምፈልገዉን ያልኩ ይመስለኛል። መጨመር ካለብኝ በሀገራችን ኢትዮጵያ ተስፋ አንቁረጥ። አንዱ በሌላዉ ወገኑ ተስፋ አይቁረጥ።

በሀገራችን ብዙ ችግሮች አሉ። ችግሮቻችን የተወሳሰቡ መሆናቸዉ፣ እየተደራረቡ መሄዳቸዉ ያሳስበኛል። ነገር ግን በዕድላችንና በአገራችን ተስፋ ከቆረጥን የሞት ሞት ነዉ። ስለሆነም ጨለምተኛ ነገሮችን እያስወገድን «ችግሮቻችን እንዲፈቱ ምንድን ነዉ ማድረግ ያለብን» ብለን ጥያቄ እያነሳን ብንወያይ፣ ብንመካከር፣ በመሀከላችን ያለዉን የድርጅት፣ የብሄር፣ የፖለቲካ አጥር ሳይገድበን ተቀራርበን እንድንሰራ ነዉ የምጠይቀዉ።

ገዢው ፓርቲ ይህንን ነገር ቢያጤነዉና ገንቢ አስተዋጽኦ ቢያደርግ በጣም ጥሩ ይሆናል። ገዢዉ ፓርቲ ከያዘዉ ግትርነት ወጥቶ ሰከን ባለ መንገድ ነገሮችን እንዲያይ እመክራለሁ።

ይሄ እንዲህ እንዳለ ሆኖ የሀገራችን እድል በገዢዉ ፓርቲ ብቻ እንዲወሰን መፍቀድ የለብንም። ሌሎች ኢትዮጵያዉያኖች ያለዉን ሁኔታ ለማስተካከል ሚና የመጫወት ድርሻ አለብን። ሁላችንም የየራሳችንን ድርሻ ካልተወጣን እየንዳንዳችን በልጆቻችን በመጪዉ ትዉልድ ተጠያቂ መሆናችን አይቀርም።

ስለዚህ ይሄ መድረክ የሕብረት ብቻ አይደለም። የኦፍዴን አይደለም። የአረና አይደለም። የኢትዮጵያዉያን ነዉ። ሁላችንም የምንወያይበት ነዉ። ይኼ ዉይይት በድርጅቶች ብቻ ሳይታጠር እያንዳንዳችን በምንኛዉም ቦታ እየተወያየን በተለይ ወደፊት መጓዝ አለብን ማለት ነዉ የምፈልገዉ።

***ሃራምቤ - አምሰግናለሁ።***